# አባ አጋግዮስ

## "ዘአፍቀርከ ወርቀ አምህሰከ ወርቀ"

## "የወደድከውን ወርቅ አቅልጪ እግትሀለሁ!"


**ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ**

nigatuasteraye@gmail.com


**መስከረም ፳፻፮ ዓ.ም**

*ማሰሰቢያ፡-* የደመራ በዓል በአገራችን መከበር ከተጀመረ ጀምሮ የጥንት ኢትዮጵያውያን ለደስታም ለመከራም ጊዜ እንዴ እንደተ ጠቀሙበት ከዚህ ቀደም ገልጪ ነበር *[ያቀረብኩትን ሙሉ ሀሳቡን ለማግኘት ይህን ሰንሰለት ይጫኑ፡-ደመራ* http://medhanialemeotcks.org/wordpress/wp-content/uploads/2011/11/Demera.pdf*]*። በዚህ ዓመት ደግሞ ከዚህ በታች ባቀረብኩt ክታብ መግቢያ ላይ እንደገለጽኩት፤ የዘንድሮውን የደመራ ያከባበር ስርአት ያዩ የውጭ ዜጋ ስለ አከባበሩ ያቀረቡልኝጥያቄ፤ የደመራውን በዓል ታሪካዊ መሰረት ስለቀሰቀሰብኝ እንደሚከተለው አቀረብኩት።

# መግቢያ

ባለፈው ሳምንት የዘንድሮውን የደመራ በዓል አከባበር በዜና ማሰራጫዎች የተመለከቱ ግሪካዊ ቄስ ባነሱት ጥያቄ የተቀሰቀሰብኝን ስሜት፤ ለዚህች ክታብ መግቢያ ላደርገው ፈለኩ። "ባገርህ የተደረገውን የመስቀሉን በዓል በመገናኛ ዘዴወች አይቼው በጣም ደስ ይላል። ሄደህ ነበር? ብለው ጠየቁኝ። "አልሄድኩም" አልኳቸው። "ለምን አልሄድክም? ብለው መልሰው ጠየቁኝ። ያሰለቼኝ ጥያቄ ስለሆነ የጥያቄቸውን መስመር በመቀየር "እርስዎን ምኑ ነው ያስደሰተዎ? ብየ ጠየኳቸው። "አከባበሩ ደስ ይላል" አሉኝ። "የእርሰዎ መንፈስ የተማረከው ባከባበሩ መብልጭልጭ ነው። የኔን መንፈስ የሚማርከው ደግሞ በበዓሉ የሚወሱት እነ ቆስጠንጢኖስ፤ ዲዮቅልጥያኖስ፤ እነ ቅድስት እሌኒና የአባ አጋግዮስ አስከፊ ባህርይ ነው። ከዚህም ጋር ደመራ

የሚለው የበዓሉ መጠሪያ እንደሚያመለክተው፤ ከልጅነት ጀምሮ ለበዓሉ የክብር መርገፎች በቤተ ክርስቲያናችን እና በየመንደሩ የሚዘመሩት፤ በየቤቱ የሚከናወኑት ድርብርብ ውበት ሰጭ ባህሎች ናቸው። ይህ የተከበረው ቅዱስ በዓል እርሰዎን ለመሰሉ ለውጭ ሰዎችና ታሪኩን ሳይገነዘቡ በብልጭልጭታው ብቻ የሚነዱትን ወገኖች ለማምታት መሳሪያ በመሆኑ እጅግ አያዘንኩ ነው” አልኳቸው።

ይህ ንግግሬ ሳባቸውና “ምን ማለትህ ነው?” ብለው ጥየቁኝ። ይህ የመጨረሻ ጥያቄያቸው ኢትዮጵያዊ ብሶቴን እንደዘረገፍላቸው እድል ሰጠኝ። “የበዓሉን ስርአት የሚመሩት ሰዎች የሚሰሩት ተግባር ከበዓሉ ጋራ የማይገናኝ አጋግዮሳዊ ሸፍጥ ነው። ምንኩስናን የሚያስነቅፍ የሚያስጠላና ቤተ ክርስቲያንንም የሚጎዳ ነው” አልኳቸው። ደንግጠው ደንቋቸውም “It is interesting” ብለውኝ ተለያየን።

ከሳቸው ጋራ የነበረኝ ንግግር በበዓላት አከባበራችን በሚቀሰቅሱት ህዝባውያን ስሜቶችና ግርግሮች “interesting” ብለው የውጭ ታዛቢዎች ከማለፍ በቀር፤ የተሸከሚቸውን ቁም ነገሮች እንደማይረዷቸው አስገነዘበኝ። እኛም ብንሆን የምናከብራቸው በዓላት በውስጣቸው የተሸከሙትን ቁም ነገር ሳናውቅ በመብለጭለጫቸው ብቻ የምንረካ ከሆነ፤ ዘመንን ከዘመን፤ ታሪክን ከታሪክ፤ ትውልድን ከትውልድ ጋራ አነጻጽረን የምንደርስበት ውሳኔ እንደማይኖረን ተሰማኝ።

ቤተ ክርስቲያናችን ደመራው ያዘለውን መሰረታዊ ታሪክ እና የመሳሰሉትን መዛግብት ያስቀመጠችልን፤ ለመጽደቅ ሳይሆን ለሥጋዊ ጥቅም ብቻ ብለው የሚመነኩሱ የሚቀሱ እንዳሉ አንብበን እንድንረዳ ነበር። የቤተ ክርስቲያናችንን መርሆ ያልተገነዘቡ ሰዎችም፤ እንደ አባ አጋግዮስ ያሉ መነኮሳት ሲገጥሟቸው እንዳይበረግጉ፤ ወይም እግዚአብሔር ይቅጣው ብለው ታዝበው እንዳይተውም ለመምከር ነበር። ከገዳም ወጥተው በየቦታው በየ አገሩ ያሉ መነኮሳት በሚፈጽሙት ደባ የዘመኔ ትውልድ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያኑ እንዳይበረግግ፤ ይልቁንም ከኛ በፊት የነበሩ ኢትዮጵያውያን ይህን የመሰሉ መነኮሳት ቢገጥሟቸው ምን ይሉ ነበር? የሚለውን ጥያቄ አንስቶ፤ የራሱን ድርሻ ይወጣ ዘንድ አደራ ለማለት እና፤ ዘመኔ ያሸከመኝን ድርሻ እራሴም ለመወጣት ይህችን ክታብ አዘጋጅቼ ለማቅረብ ወሰንኩ።

# ደመራ ከኋላው ያዘለው መሠረታዊ ታሪክ

በያመቱ እየተመላለሰ የሚከበረው ደመራ በየዘመኑ የገጠሙትን ክስተቶች እያዘለ ከኛ የደረሰ አስገራሚ ከምንላቸው ከታሪካውያን አንጓወች አንዱ ነው። ደመራውን ስናስታውስ መስቀሉን ፈልጋ ያገኘችው ቅድስት እሌኒ ትታወሳለች። የቅድስት እሌንን ታሪክ ስንከተል መስቀሉን በማፈላለጉ የረዳት እና “የተዘጉ አብያተ ክርስቲያናት ይከፈቱ” ብሎ ያወጀው ቆስጠንጢኖስ ብቅ ይላል። የቆስጠንጢኖስን ታሪክ ስንከተል ደግሞ፤ አብያተ ክርስቲያናት እንዲዘጉ ምክንያት የሆነው አባ አጋግዮስንና፤ “ቤተ ክርስቲያን ይዘጉ” ብሎ ያወጀውን ዲዮቅልጥያኖስን ስቦ ያመጣቸዋል።

በዚህ ዘመን ያለን ኢትዮጵያውያን ከደመራው በዓል ለመማር ፈቃደኞች ከሆን፤ የደመራው ታሪክ የሚያስተምረን ጥልቅ ግንዛቤ ተሸክሟል። ቤተ ክርስቲያን ዘጋ ተብሎ በታሪክ የሚከሰሰው አባ አጋግዮስን ወርቅ ግቶ የገደለው ዲዮቅልጥያኖስ ነው። ዲዮቅልጥያኖስ እጅግ በመደነቅ ላይ ካለው ከቆስጠንጢኖስ የሚወዳደር እምነትና ታሪክ ባይኖረውም፤ ዲዮቅልጥያኖስ በክርስትና አማኞች በተለይም በመነኩሴ ላይ የነበረው እምነት ጥልቅ እንደነበረ ከታሪኩ መረዳት ይቻላል።

ዲዮቅልጥያኖስ የሚያስተዳድራትን አገር በሚያጎራብቷት አገሮች መካከል ጦርነት ተነሳና የዲዮቅልጥያኖስ የልብ ወዳጅ የሆነው ንጉሥ ቴዎድሮስ የተባለው ጦርነቱን አሸነፈ። ቴዎድሮስ ንጉሥ ዲዮቅልጥያኖስን ከልብ ያምነውና ይወደው ስለነበረ የደስታው ተካፋይ ይሆን ዘንድ በጦርነቱ ላይ የማረከውን ኒጎምዶስን፤ ለሚወደው ለዲድዮቅልጥያኖስ እንደሰለባ አድርጎ ሰጠው። ዲዮቅልጥያኖስ የተማረከውን ኒጎምዶስን አይቶ ጥንካሬውንና ወጣትነቱን ተመለከተ። ቢማር ወደፊት የሰላም የፍቅር የእውቀትና የማስተዋል ምንጭ በመሆን ለራሱ ህዝብም ሆነ ለሌውም ዜጋ ይጠቅማል ብሎ አሰበ። ሀላፊነቱን ወስዶ ለዚህ ታላቅ ተልእኮ ኒጎምዶስን የሚያበቃው ታማኝ አስተማሪ ማነው ብሎ አካባቢውን ቃኘ።

በዘመኑ ያካባቢውን ቤተ ክርስቲያን የሚመራ አባ አጋግዮስ የሚባል መነኩሴ ነበር። ይህ መነኩሴ "ታማኝ ሁኑ! አትዋሹ! ገንዘብ አትውደዱ! ከሥጋ ፈቃድ ሽሹ!" እያለ ስለሚያስተምር፤ ከዚህ ቅዱስ መነኩሴ ሌላ ይህን ሀላፊነት ሊወጣ የሚችል የለም ብሎ ዲዮቅልጥያኖስ አሰበ። "አጠንክረህና ደጋግመህ ለህዝብ የምትነግረውን ግብረ ገብ እምነትና ሞራል አስተምረው" ብሎ በሰለባ የተቀበለውን ኒጎምዶስን ለአባ አጋግዮስ ሰጠው።

የኒጎምዶስ ወገኖች ኒጎዲሞስ ይኑር ይሙት ሲያጠኑ፤ እንዳልተገደለ ለዲዮቅልጥያኖስ የምርኮ ሰለባ ተደርጎ እንደተሰጠ ተረዱ። ማፈላለጋቸውን ቀጠሉና ዲዮቅልጥያኖስም ለመነኩሴው ለአባ አጋግዮስ አስተምረው ብሎ ባደራ እንደሰጠው ደረሱበት። ወደ አባ አጋግዮስ ሄደው " በምርኮ የተሰጠህ ኒጎዲሞስ ወገናችን ነውና ስጠን" ብለው ተማጸኑት። መጀመሪያ አባ አጋግዮስ "አደራ ጥብቅ ሰማይ እሩቅ" እንዲሉ በአደራ የተሰጠኝን ለናንተ አሳልፌ እንደሰጣችሁ እንዴት ደፍራችሁ ጠየቃችሁኝ! እኔ እኮ መነኩሴ ነኝ። አደራ የሚበላ ከሀዲ መስላኳችሁ? ብሎ በቁጣ ጮኸባቸው። ወገናቸውን ማግኘት ባለመቻላቸው ተስፋ ቆርጠው እያዘኑ ወደ አገራቸው በመመለስ ላይ ሳሉ፤ አብሮ በመኖር የአባ አጋግዮስን ዝቃጭነት ያውቅ የነበረ የራሱ የአባ አጋግዮስ ቆሞስ (ተላላኪ) ሰዎችን ተከትሎ ሄዶ " የምትፈልገውን እንሰጥሀለን ብትሉት ይሰጣችኋል" ብሎ ነገራቸው። እነሱም ቆሞሱ እንደነገራቸው አደረጉ። አባ አጋግዮስ የስጦታን ነገር ሲሰማ "አደራ ጥብቅ፤ ሰማይ እሩቅ" እያለ የፎከረውን ወዲያውኑ ዘነጋና "የምትሰጡኝን አሳዩኝ?" አላቸው። እነሱም በዘመኑና ባካባቢው ውድ የነበሩ ነገሮችን የሀር ልብሶች እና ወርቅ ሰበሰበው በማምጣት ከፊቱ አፈሰሱለት "ወሶበ ርእየ ወርቀ ወብሩረ ወሜላተ ስህወ ልቡ ከመ ሰም ወኮነ ዝሁለ አዕምሮ" ማለትም፡-አባ አጋግዮስ ወርቁን ብሩንና ግምጃውን ባየ ጊዜ ልቡ እንደ ሰም ቀለጠ። አዕምሮውን ሳተ፡ በአደራ ከሰጠው ከዲዮቅልጥያኖስ ደብቆ የተማረከውን ኒጎዲሞስን አሳልፎ ሰጣቸው።

ኒጎዲሞስ ወደ አገሩ ተመልሶ ከህዝቡ ጋራ ከተቀላቀለ በኋላ፤ ህዝቡን አስተባብሮ እንደገና ጦርነት ከፈተና ማርኮት ከነበረው ከንጉሥ ቴዎድሮስ ጋራ መዋጋት ጀምረ። ንጉሥ ቴዎድሮስ ለሁለተኛ ጊዜ እንደቀድሞው ማረከው። አቅርቦ ሲያየው ከዚያ በፊት ማርኮ ለወዳጁ ለንጉሥ ዲዮቅልጥያኖስ የድል ሰለባ አርጎ የሰጠው ሰው መሆኑን ተረዳ። "ከዚህ በፊት በተካሄደው ጦርነት ማርኬህ የነበርከው አይደለህም? ብሎ ጠየቀው። ኒጎዲሞስም "አዎ ነኝ" አለው። "ታዲያ እንዴት ዞረህ መጣህ? ብሎ ጠየቀው። ኒጎዲሞስ ወገኖቹ ከአባ አጋግዮስ በብዙ ወርቅ ታድገው እንደመለሱት ነገረው።

ቴዎድሮስም፡-

> "የምርኳችን ሰለባ አርገን የሰጠንህን ኒጎዲሞስን መልሰህ ለጠላታችን በመስጠትህ እጅግ አዝነናል። ተመልሶ ህዝቡን አደራጅቶ በከፈተብን ጦርነት ከኛም ከሱ ወገንም ብዙ ሰው አለቀ። በዚህ ጦርነት ላለቀው ህዝባችን የምናዝነው ባንተ ነው። ባትገለው እንኳ በግዞት ማስቀመጥ ሲገባህ፤

*እንድንቋቋመው የሚያስችለንን ዝግጅት እንዳናደርግም ከኛ ደብቀህ ለጠላቶቻችን መልሰህ በመስጠትህ የተዋጋሀን አንተነህ"*

ብሎ ንጉሥ ዲዮቅልጥያኖስን ወቀሰው። ዲያቅልጥያኖስም አስተምሮ የሞራል የእምነት የሰላም ሰው ያደርገዋል ብሎ ያመነው አባ አጋግዮስ የተባለው መነኩሴ ይህን ደባ በመፈጸሙ እጅግ አዘነ። ተበሳጨ።

ዲዮቅልጥያኖስ አባ አጋግዮስን ጠርቶ፦

*"እንድታስተምረው ባደራ የሰጠንህን ሰው አምጣው፤ እንዳይርበው እንዳይጠማው እንዳይበርደው ለሰውነቱ ያደረክለትን ጥንቃቄ እንየው። መክረህ አስተምረህ በሞራል የገነባሀውንም ብስለት እንፈትሸው። ላደረከውም መልካም ነገር ሁሉ ሊደርግልህ የሚጋባውን ሽልማት እንሰጥሀለን" አለው። አባ አጋግዮስ አሳልፎ የሰጠው ሰው እንደገና መማረኩንና ዲዮቅልጥያኖስም መወቀሱን አላወቀም። <u>በምንኩስናው ተሸፍኖ የሚያደርገውን ማታለል ቀጠለና፤ "እሱማ ሞቶ ከተቀበረ ሶስት ቀኑ ነው። ካላመንከኝ ሬሳውን ላሳይህ"</u>*

በማለት በዘቀጠ ንግግሩ አደበስብሶ ሊያልፈው ሞከረ። አሁንም ሊያታልለው በመሞከሩ የዲዮቅልጥያኖስ ቁጣ በአባ አጋግዮስ ላይ የበለጠ እንደ እሳት ነደደ። "ሬሳውን ማሳየትህ ይቅርና በምታምነው በምታገለግለው አምላክ ምለህ መሞቱንና መቀበሩን ታረጋግጥልኛለህ?" አለው። እንዲምል ያቀረበለትን መሀላ ተቀብሎ ምንም ሳያቅማማ ግጥም አርጎ እንደውሀ ጠጣት። ባካባቢው ካሉት ሁሉ ሰዎች የበለጠ አምኖ የሰጠውን አደራ በገንዘብ መሸጡ፡ <u>የራሱን አምላክም ክዶ ሲምል ሲያየው በአባ አጋግዮስ ምንኩስና የተሸፈነው ኃጢአት ለሰማይና ለምድር የከበደ እንደሆነ ዲቅልጥያኖስ ተረዳ።</u>

*<u>"የተሸፈነው ኃጢአትህ ቢገለጥ የማያልቅ ጉደኛ ሰው ነህ። በሌላ ነገር ከሌላ ጋራ በመሞዳሞድ በግፍ ገለህ የቀበርከውን ሬሳ ካንተ ጋራ አልጎትትም"</u> ብሎ በቁጣና በብስጭ ከተናገረ በኋላ፤ ይህን አታላይ መነኩሴ በምን ልቅጣው ብሎ አሰበ። ይህንን የመሰለ የተደራረበ ኃጢአት በመፈጸም ላይ ያለውን ግለ ሰብ አንድ ወንጀል በፈጸመ ተራ በደለኛ ላይ በሚሰነዘሩት የቅጣት አይነቶች ግርፋት፤ ስቅላት፤ እና እስራት መቅጣት የሚመጥኑት አይደሉም። ከነዚህ የቅጣት አይነቶች ባንዱ ብቀጣው፤ የፈጸመውን በደል ተራ ከማድረግ ባሻገር፤ ከሚያመልከው አምላኩ በቀር ተከላካይ የሌለውን መነኩሴ ገደለ ተብየ መወቀስ <u>አልፈልግም። ራሱ የሚያመልከውን አምላክ በካደበት፤ ተሰገብግቦ የራሱን ክብር ያዋረደበትን ወርቁን አቅልጬ ባጠጣው፤ ራሱ የመረጠው ወርቅ ገደለው ስለሚባል ከታሪክ ተወቃሽነት ነጻ ያደርገኛል"</u> ብሎ ወሰነ።*

ባካባቢው ያሉትን የወርቅ አንጥረኞችን ጠርቶ ወርቅ በማቅለጥ ወደፈሳሽነት እንዲለውጡለት አደረገ። አባ አጋግዮስን "<u>"ዘአፍቀ ወርከ ወርቀ አምህሰከ ወርቀ"</u> ብሎ የቀለጠውን ወርቅ ጋተው። አባ አጋግዮስ እዚው ላይ ተንፈራፍሮ ሞተ። ዲዮቅልጥያኖስ ቀጠለና "አባ አጋግዮስ የሚያመልከው የሚታመን አይደለም ። <u>እሱ በሚመራው ድርጅት የተሰገሰጉት መነኩሴዎችም በማስመሰል ወርቅ ለመዝረፍ እንጅ ለህዝቡ በሚናገሩት የሚመሩና የሚያምኑ አይደሉም። እነዚህን በመሳሰሉ አባ አጋግዮሶች የሚመሩ ቤተ ክርስቲያኖች ይዘጉ" ብሎ አወጀ።</u> የደመራ ታሪካዊ መነሻ ባጭሩ ይህ ነው። ታዲያ ከኛ በፊት በነበሩት ሰዎች ዘመን ይህ ድርጊት በኢትዮጵያ ቢፈጸም ኖሮ ምን ይሉ ነበር? እንድጽፈው ያስገደደኝም "ምን ይሉ ነበር? የሚለው ጥያቄ ነውና አብረን እንሂድበት።

# አባቶቻችን በኛ ዘመን የሚፈጸመውን ጉድ ቢያዩ ምን ይሉ ነበር?

ቅዱስ ያዕቆብ "እመ ቦ ዘያጸምእ ለቃል ወኢይገብሮ ይመስል ከመ ብእሲ ዘይሬኢ ፍጥረተ ገጹ በመጽሄት። ወጠይቆ ርእሶ ኀለፈ ወረስዐ ዘከመ እፎ ውእቱ" (ያዕ"፩፡ ፳፫—፳፭) ማለትም፡-"ምክር፤ ታሪክ ሰምቶ የራሱን ስህተት ለማስተካከል የማይጥር ሰው፤ መስተዋት በፊቱ ዘርግቶ በፊቱ ያለውን ጉድፍ የማያነሳ አላማ ቢስ ይመስላል።" እንዳለው፤ የተጻፈ ታሪክ የሚረዳን እራሳችንና ባካባቢያችን ያለው ህብረተ ሰብ የሚያደርገውን የታሪክ ሂደት አነጻጽረን ያፈነገጠውን እንድናርምበት ነው። በጠበንጃ ታፍኖ በአገር ውስጥ ላለው ዜጋ ፋታ ልስጠውና፤ ይህች ክታብ በነጻው ዓለም ባሜሪካ በካናዳና በእንግሊዝ አገር በምንኖር ክርስቲያኖች ላይ እንድትነጣጠር እፈልጋለሁ። ቤተ ክርስቲያናችን ስለ አባ አጋግዮስ መዝግባ ያስቀመጠችልንን ታሪክ አጉልቶ እንደ ሚያሳይ መነጽር በአይነ ልቡናችን ሰክተን፤ በሩቅ እና በየአካባቢያችን ያሉት አንዳንድ ካህናት በተለይም መነኮሳት ጳጳሳት ነን እያሉ የሚፈጽሙትን አጋግዮሳዊ ባህርይ እንመዝንበት።

ለመመዘን ስንሞክርም "አንትሙሂ ወኢትጻኡ እምቃለ መጻህፍት ከመ ኢትትዐበዩ ላእለ ቢጽክሙ"(፩ኛ ቆር ፬፡ ፮) ማለትም፡- አንዳንድ ጊዜ በምቀኝነት ባድማ በንጹሀን ሰዎች ላይ የሚፈጸሙ ግፎች በደሎች እንዳሉ ሳንረሳ፤ ስንደግፍም ስንቃወምም ቤተ ክርስቲያናችን በግምጃ ቤቷ ሰብስባ ከያዘቻቸው መጻሕፍት እንዳንርቅ መጠንቀቅ ይኖርብናል። በቅድስት ቤተ ክርስቲ ያናችን ዙሪያ የሚከሰቱትን ውስብስ ነገሮችን ሁሉ ለመፍታት ወደ ምንኖርባቸው አህጉር ህግጋት ከመውሰዳችን በፊት፤ ይህች ጥንታዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በሰጠችን መመሪያ መዝነን መወሰን አለብን።

ቤተ ክርስቲያናችን "ወኲሎ ዘይትቃወም ዘንተ ዘአቅደምነ ወተናገርናሁ ተቃዋሚሁ ለግዚአብሔር ውእቱ። ይህስስ ዘንተ ውስተ መጻህፍተ እግዚአብሄር። ወይነጽር ውስተ መዛግብተ ቤተ ክርስቲያን አሜሃ የአምር ከመ እግዚአብሔር አዘዘነ ዘንተ ኲሎ"(ሃ አበው ፳፪፡ ፲፭) የሚል ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ሰጥታናለች። ይህም ማለት፡- "ቤተክርስቲያናችን አዘጋጅታ እንድንመራበት ከሰጠችን መመሪያ ጋራ የሚጋጭ፤ ከእግዚአብሔር ጋራ መጋጨቱን መርሳት የለበትም። ቤተ ክርስቲያን በመመሪያዋ መሰረት የምትወስናቸውን ውሳኔዎች ዓለማዊ ዳኛ በይግባኝ ሰሚ ዳኝነት ለመተቼት ከመሞከሩ በፊት፤ ቤተ ክርስቲያናችን በግምጃ ቤቷ ሰብስባ የያዘቻቸውን መጻሕፍት ይመርምር። ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ካዘዘን ውጭ እንዳልሰራን ይረዳል። ውሳኔያችንንም አድንቆ ያከብራል።" ይላል።

ብዙ አይነት ወንጀል በሚፈጸምበት ገንዘብ ላይ "we trust in Lord" የሚል አርማ ያስቀመጠ ያሜሪካ ህግ፤ በድርጅት መካከል ይህን የመሰለ ግጭት ተከስቶ ሲቀርብለት "መመሪያህ ምን ይላል እንጅ፤ አባ አጋግዮስ ምን ይላል" አይልም። ራሳቸው የሰሩትን ህግ እየደመሰሱ የራሳቸውን ህዝብ ከሚያሰቃዩ ወንጀለኞችና እና አምባ ገነኖች መንግሥታት ሁሉ የአሜሪካን መንግሥት ልዩ ያደረገውና እኛም የተጠጋነው በዚህ አስደናቂ መመሪያው ነው። ቤተ ክርስቲያናችን መዝግባ ያስቀመጠችውን ቅዱስ መመሪያችንና ያሜሪካን የከናዳን እና የእንግሊዝን ህግ ያልተረዱ እነ አባ አጋግዮስ፤ ዘሞታችሁ ዘረፋችሁ ሲባሉ ከማፈርና ለንስሀ ከመዘጋጀት ይልቅ፤ እጉም አስጥሉን እያሉ ወደ ዓለማውያን ፍግጋት ይጠጋሉ። አድኑን ብቻ አይደለም። ንስሀ ግቡ ብለውናልና ሚሊዮውን ዶላር ካሳ እንዲሰጡን ምእመናን አስገድዱልን እያሉ የሚማጸኗቸው ህግጋት፤ አስመስሎ ማታለልን አጥብቀው የሚቃወሙ መሆናቸውን ባለመገንዘብ እንደ አባ አጋግዮስ ራሳቸውን በራሳቸው እየጠለፉ ነው።

"ከአያያዝ ይቀደዳል፤ ካነጋገር ይፈረዳል" እንዲሉ፤ በየቦታው የተቃውሞ ድምጽ ምታሰሙ ሁሉ ምእመናን በመነኮሳት በጳጳሳትና በኔ ቢጤ ቀጣፊ ላይ ጣት ለመጠቆም ከመሞከራችሁ በፊት፤ በራሳችሁ ላይ እንዳይባርቅባችሁ፤ ከላይ እንደተገለጸው ከቤተ ክርስቲያኒቱ መመሪያ ዝንፍ አለማለታችሁን ማረጋገጥ አለባችሁ።

በክርስትና ስም ገንዘብ እየሰበሰበ የራሱን ጥሪት ያከማቻል። በየሳምንቱ የተለያዩ ልብሶች እየቀያየረ ያጌጣል። ዝሙት ይፈጽማል። የሰው ትዳር ያፈርሳል። እየተባለ የሚወቀሰው ሁሉ፤ የተወቀሰበት ጉዳይ እንዲጣራ፤ ይጣራ ብለው ድምጽ የሚያሰሙትን ምእመናን መደገፍ ይገባል። ከመደገፍ ይልቅ "እኛ ምን አገባን እግዚአብሄር ይጉዳው" እያሉ ቆሞ ማየት የክርስቲያን ባህርይ አይደለም። ይህን የመሰለ ደባ በቤተ ክርስቲያን ላይ የፈጽመውን በገንዘብም ሆነ በድምጽ ለመደገፍ መሞከር፤ እነ አባ አጋግዮስን የበለጠ ማጠናከርና ማበረታታት እና፤ አባ አጋግዮስ በፈጸመው ደባ ዲዮቅልጥያኖስን በወዳጁ እንዲወቀስ ያስደረገውን ተግባርም መልሶ መድገም ነው።

*"የምርኳችን ሰለባ አርገን የሰጠንህን ኒኅዲሞስን መልሰህ ለጠላታችን በመስጠትህ እጅግ አዝነናል። ተመልሶ ህዝቡን አደራጅቶ በከፈተብን ጦርነት ከኛም ከሱ ወገንም ብዙ ሰው አለቀ። በዚህ ጦርነት ላለቀው ህዝባችን የምናዝነው ባንተ ነው። ባትገለው እንኳ በግዞት ማስቀመጥ ሲገባህ፤ እንድንቋቋመው የሚያስችለንን ዝግጅት እንዳናደርግም ከኛ ደብቀህ ለጠላቶቻችን መልሰህ በመስጠትህ የተዋጋህን አንተነህ"* ብሎ ንጉሥ ቴዎድሮስ በዲዮቅልጥያኖስን ላይ የሰነዘረውንም ወቀሳ ልንረሳው አይገባም።

ታሪኩ እንደሚያስረዳው፤ ዲዮቅልጥያኖስ በአባ አጋግዮስ ክህደት ተበሳጭቶ "አብያተ ክርስቲያናት ይዘጉ" ብሎ ቢያውጅም፤ በክርስትና አማኞች በተለይም በመነኩሴ ላይ የነበረው እምነት ከባድ እንደነበረ ከሰጠው ጥብቅ አደራ መረዳት ይቻላል።

ታዲያ በአብያተ ክርስቲያናት መዘጋት መወቀስ ያለበት ዲዮቅልጥያኖስ ነው? ወይስ አባ አጋግዮስ? ዲዮቅልጥያኖስን አባስጭቶ ቤተ ክርስቲያን እንዲዘጋ ያደረገው የታላቁ ከሀዲ ያባ አጋግዮስ ደባ ተሸፍኖ፤ ቤተ ክርስቲያን ዘጋ እየተባለ የሚወቀሰው ዲዮቅልጥያኖስ ነው ። ዲዮቅልጥያኖስማ አባ አጋግዮስ ይክደኛል ብሎ ሊጠራጠር ይቅርና የተማረከውን ሰው ጦርነት ተገቢ አለመሆኑን አስተምሮ የሞራል የእምነት የርህራሄ የሰላም ሰው ያደርገዋል ብሎ በአደራ በመስጠት አባ አጋግዮስን ያመነ ገራ ገር ሰው ነበር። እነ አባ አጋግዮስ በፈሉበት ይህን በመሰለ ዘመን ደመራ ሲከበር፤ ያአባ አጋግዮስ ታሪክ በግልጽ ለህዝብ መነገር ነበረበት።

አባ ማትያስ መነገር ያለበትን ያባ አጋግዮስን ታሪክ ሰውረው፤ "ወእለኒ እጉዛን በቅኔ መሪር አምላክነ አድኅኖሙ በምህረትከ (ቅ ሐዋ ገጽ ፺፩ ቁ ፳)" ብሎ መጽሀፋችን በሚያዝዘን መሰረት በእስራት ላይ ያሉትን ዜጎች እግዚአብሄር ያስፈታችሁ የሚል ቃል የሌለበት ቃለ መርገም አሰሙ። መንግሥት "የህግ ታራሚዎች" እያለ ተቃዋሚወቹን በሚፈርጅበት ቋንቋ "የህግ ታራሚዎች ሆናችሁ በየማረሚያ ቤቱ የምትገኙ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት" በማለት ያቀረቡት ንግግር መንግሥትን የሚሸፍን በሸፍጥ የተሞላ በመሆኑ ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ቃለ መርገም እንጅ፤ ቃለ በረከት ሊሆን ፈጽም የሚችል አይደለም።

ኢትዮጵያውያን ሁሉ ታዘቡ! አንዲት ቀን እንኳ ተሳስተው የታሰሩትን እግዚአብሄር ያስፈታችሁ ብለው የማያውቁ ሰው ናቸው። መንግስት በራሱ ሃይል በቦታው ላይ ያስቀመጣቸው የሚሰራውን ሁሉ ደባ ሸፍነው እና ገልብጠው ለዓለም እንዲያቀርቡለት ነው። እንደነዚህ ያሉትን አጋግዮሳውያን ባህርይ አውቆ የሚገልጸው አብሮ የኖረ የኔ ቢጤ ተላላኪ (ቆሞስ) ብቻ ነው። የዛሬውን አቋማቸውን ባላውቅም የአባ ማትያስ ቆሞስ የነበሩት፤ አባ

ሰረቀ “እውነትና ንጋት” በሚል ርእስ በመጽሀፍ መልክ ያቀረቡባቸው የመዛግብት ስብስብ፣ እኛ የተፋልምንባቸው የአባ ማትያስን አጋግዮስነት የሚያረጋግጡ ናቸው።

ህዝቡ ለተቀደሰው አገልግሎት እንዲውል የሰጠውን ገንዘብ፣ በፓትርያርኩ ምርጭ ጊዜ መንግስት ወደ አዘጋጀው እንቅስቃሴ እንዲፈስ ያደረገው፣ በንጹሐንን ዜጎች ላይ “የህግ ታራሚዎች” እያለ የሚፈጽመውን ስቃይ ሸፍኖ፣ ጽፎ የሚሰጠውን በየበዓላቱ የሚያስተጋባለት እንደ አባ ማትያስ ያለውን የገደል ማሚቶ ለማስቀመጥ ነበር። ከንሳስ ላይ መጥተው ዘባርቀው ከሄዱ ጀምሬ ባላማቋረጥ ስማቸውን እየጠቀስኩ በጻፍኩባቸው ጦማሮች አንባቢን እስኪሰለቸው ድረስ እናገር የነበረውም፣ ለነበሩበት ቦታ ብቃት አልባነታቸውን ለመናገር ብቻ ሳይሆን፣ የገደል ማሚቶ በመሆን ቤተ ክርስቲያንና በጠቅላላ የሀገሪቱን ዜጋ ከመበደል የማይመለሱ መሆናቸውን ለመግለጽ ነበር። ብቃት እንደሌላቸው እያወቁ ተቃውሚችንን ጥሰው እንዲገቡ ያደረጋቸው፣ አባ አጋግዮስን አፈንድቶ የገደለው ብልጭልጭ ልብሱና በፊቱ ላይ የፈሰሰው ወርቅ ነው።

ንዋይ በካህናት በተለይም እሳቸውን በመሰሉ መነኮሳት እጅ ከገባ አይነ ልቡና አሳውሮ አደራ የሚያስበላ፣ ክብርን የሚያስረሳ፣ ጠቅላላውን ህብረተ ሰብ የሚያፈዝ የሚያደነዝዝ አዚም ነው። ይህም በመሆኑ ክርስቶስ ተከታዮቹን ሀዋርያት “ኢታጥርዩ ለክሙ ወርቀ ወብሩረ ወኢጸሪቀ ውስተ ቅናውቲክሙ”( ማቴ ፲ ፡ ፱) ብሎ አስጠነቀቃቸው። ቅዱስ ጳውሎስም ለደቀ መዝሙሩ ለጢሞቴወስ:-“እስመ ሥርው ለኩሉ እኩይ አፍቅሮ ነዋይ። እስመ ቦ እለበዛቲ ስህቱ ወዐለው ሃይማኖቶሙ ወኀሠሡ ለርእሶሙ ብዙኃ መቅሰፍተ።( ፩ኛ ጢሞ ፮፡ ፲—፲፫)” ብሎ አስጠነቀቀው። ማለትም:- “የክፋት የውድቀት የጥፋት ሁሉ ምንጭ ገንዘብ መውደድ ነው። ገንዘብ የወደዱ ሁሉ ታማኝነታቸውን ክብራቸውን አጡ። ያሳበዳቸው የገንዘብ ፍቅር ባልተጠበቀ መቅሰፍት ራሳቸውን እንዲያጠፉ አደረጋቸው” ይህን አንድም እያሉ ያስተማሩኝ የደብረ ሊባኖሱ የሐዲስ ትርጓሜ መምህራችን የኔታ ብርሃኑ፣ በሐዋርያት ዘመን በገንዘብ ፍቅር ምክንያት ልዩ በሆነ ቅጣት የተቀጡትን ሀናንያንና ሰጲራን ለማስረጃ ሲያቀርቡልን አባ አጋግዮስን መደምደሚያ አድርገዋል።

የሊቁ መምህር የኔታ ቢረሳውም፣ ዮሐንስ አፈወርቅ በ፩ኛ ድርሳኑ ላይ “ወእመሰ ኢይቴክዝ ለመፍቅደ ሥጋሁ አልቦ ዘይቀንዮ ወኢዘያፈርሆ። አላ ይከውን መልእልተ ኩሉ ወግዑዘ እምኩሉ፡ ወዘሰ ይሜንና ለሥጋሁ ውእቱኬ ይረክባ ። ወሰይጣንሂ እምከመ ርእያ ለነፍስ በዘከመዝ ግብር ኢይክል ቀሪበ ኀቤሃ” ብሎ የተናገረውን ማለትም:- “ለሥጋዊ ቅንጦት የማይጨነቀውን ሰው ልጓም ባፍህ ከትቼ እንደፈረስ ልጋልብህ፣ እንደ አህያ ልጫንህ፣ እንደበሬ ልጥመድህ ለማለት የሚደፍረው የለም። ይልቁንም እሱ ከሁሉ በላይ ተፈሪ እና ተከባሪ ነው። ለሥጋዊ ምኞቱ ተገዥ ያለሆነ ሰው፣ ምንጊዜም እሱነቱን ሳያጣ በክብር ይኖራል።” ብለው ሀተታቸውን የደመደሙት፣ አባ አጋግዮስ የሚወደውን ወርቅ ተግቶ ልቡ ፈንድቶ ሞተ ብለው ነው።

ዛሬ በያገሩ በከናዳ በለንደን እና ባሜሪካ ያሉ ምእመናን በመነኮሳት ላይ የምታሰሙት ጩኸት ምነናው (ምንኩስናው) ክህነቱን የወንጌል ስብከቱ በፍቅረ ነዋይ፣ በዝሙት፣ በትእቢት እና በመሳሰሉት ከቅድስና በራቁ ስህተቶች ተተኩብን በማለት ነው።

ከሁልም በላይ ይልቅ እጅግ አሳዝኖ የሚያስቆጣው “ያቁሙ” ሲባሉ “እኔ ብቻ አይደለሁም” ከማለታቸው አልፈው፣ ንስሀ ይግቡ ያሏቸውን ምእመናን የሚሊዮን ዶላር ካሳ እንዲከፍሏቸው በዓለማዊ ዳኛ መክሰሳቸው ነው። “ይደለወነ ካዕበ ከመ ኢንጽልኦሙ ለእለ ይነሥኡነ በጽልእ ወቀትል በእንተ ምንትኒ እምንዋይነ” (አንቀጽ ፲ ገቢ ቁ ፫፻፶፩) ማለትም:- “በማነኛውም መንገድ ገንዘብህን የወሰደብህን ሰው መክሰስ ቀርቶ አትጥላው” ብላ መመሪያ ከሰጠችን ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ጉያ እነዚህን የመሳሰሉት መነኮሳት የመጡ ናቸው ብለን ልንቀበላቸው ፈጽሞ አይገባም። ሊቃውንት አበው እንደነዚህ ያሉትን ሰዎች ተዋቸው፣ እለፏቸው፣

ሲሉ ሰምቼ አላውቅም። በዝምታ እንለፍ የሚለውን ሰው በደሉን ከፈጸመው ይልቅ የከፋ መሆኑን ለመግለጽ “ምጽድቅ” ይሉታል። ማለትም ሊጸየፉት ሊያወግዙት ሊያስወግዱት ሲገባ፤ ሰላም ወዳድ ትሁት ታጋሽ መስሎ፤ ከዚያም ርቆ እግዚአብሔር ይቅጣው ብሎ ማለፍ ዲዮቅልጥያኖስ “ዘአፍቀርከ ወርቀ አምሀሰከ ወርቀ” ብሎ ወርቅ ግቶ አባ አጋግዮስን እንዲሞት ካደረገበት ፍርድ እጅግ ተለጥጦ የሄደ ኃጢአትና በደል ነው።

ባንዲት አጥቢያ ያሉ ምእመናን እየጮሁ፤ በተመሳሳይ እምነት አንድ የሆኑ ያካባቢው አጥቢያ ክርስቲያኖች በተለይ ካህናት ዝም ብለው የሚያልፉ ከሆነ፤ አካላቸውን ቆርጠው የጣሉ በምጽድቅ ውስጥ የገቡ መሆናቸውን መርሳት የለባቸውም። ምጽድቅ ማለትም ተመሳሳይ ስህተት በስህተት ውስጥ በመውደቁ፤ ይህን ብል፤ ሌላው አንተስ ተመሳሳይ ነገር አድርገህ የለምን እንዳይባል፤ አያገባኝም እግዚአብሔር ይክፈለው በሚል ሰንካላ ምክንያት ራስን መጋረድ ነው። ላንዲት ሳንቲም መበለጥ ትእግስት የሌለን ሰዎች ስንሆን፤ እምነትን ሞራልን ቤተ ክርስቲያንን ያክል ነገር ሲፈርስ መቃወም ሲገባ፤ እግዚአብሔር ይክፈለው ብሎ ማለፍ፤ አዕምሮ የሰጠን እግዚአብሄርን መፈታተን ነው። እግዚአብሔርን ከሚያስቆጣቸው ተግባራት አንዱ ነው። “ለኃጣን የወረደ መቅሰፍት፤ ለጻድቃን ይተርፋል” የሚባለው ህዝብ ማረም ሲችል በመመጻደቅ በሚታለፈው ይህን በመሰለ ድርጊት የሚቀሰቅሰው መቅሰፍት ነው።

እነዚህን ሰዎች እያዩ እንደፈለጋቸው ይሁኑ ብሎ በዝምታ መተው እኮ ፤ በሚወስዱት ገንዘብ ገዝተው በሚበሉት ጮማ ቅልጥማቸውን እያፈሉ፤ በሚጠጡት ውስኪና ወይን ስሜታቸውን እያስገነፈሉ ባዩዋት ሁሉ ሴት ላይ እንደ ግስላ እየዘለሉ ይፈንዱ ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያንንም ለነቃፊ አሳልፈው ይስጡ፤ ህብረተ ሰቡንም ይበክሉ፤ የተቀደሰውን ትዳር ያፍርሱ፤ ህጻናትም ወላጅ አልባ ሆነው ይደጉ ብለን መስማማታችን ነው። ግባችን ይህ ከሆነ ግን ፤ በምንኩስና ተሰውሮ፤ አብጦ የፈነዳው የኃጢአት እዥና መግል፤ ወደ ህብረተ ሰብ ተሻግሮ እንዳይበክል የወደድከው “ወርቅ ይግደልህ” ብሎ በአባ አጋግዮስ ላይ በወሰደው እርምጃ፤ ዲዮቅልጥያኖስን ከኛ የተሻል እንደሚያደርገው ልንረሳ አይገባንም።

ይቆየን።

ለሌሎች ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ጦማሮች የሚከተለዉን ድህረ-ገጽ ይመልከቱ::

http://www.medhanialemeotcks.org/